MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

# የሰራተኛ
# የስነምግባር ደንብ

Malcolm Baldrige
National Quality Award
2010 Award Recipient

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

የትምህርት ዓመት 2016-2017

MONTGOMERY COUNTY
Board of Education
MARYLAND

## ራእይ

ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ ትምህርት እንዲሰርፅ እናደርጋለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ በኮሌጅም ሆነ በስራ ስኬታማ እንዲ(ድት)ሆን አካዴሚያዊ፣ ፈጠራዊ የችግር አፈታት፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክሂሎቶች ይኖሩ(ሯ)ታል።

## ዋነኛ አላማ

ሁሉም ተማሪዎች በወደፊት ኑሮአቸው እንዲለሙ/እንዲበለፅጉ ማዘጋጀት።

## ዋነኛ እሴቶች

ትምህርት
ግንኙነቶች/ዝምድናዎች
ክብር
ልቀት
ፍትህ

## የትምህርት ቦርድ


Mr. Michael A. Durso/ሚር. ማይክል ኤ. ዱርሶ
ፕሬዚደንት

Dr. Judith R. Docca/ዶር. ጆዲት ዶካ
ም/ፕረዚደንት

Mr. Christopher S. Barclay/ሚር. ክሪስቶፈር ኤስ ባርክሌይ

Mr. Philip Kauffman/ሚር. ፊሊፕ ካውፍማን

Mrs. Patricia B. O'Neill/ወሮ. ፓትሪሻ ቢ ኦኔይል

Ms. Jill Ortman-Fouse/ወይ. ጂል ኦርትማን-ፋውዝ

Mrs. Rebecca Smondrowski
ወሮ. ሬቤካ ስሞንድሮውስኪ

Mr. Eric Guerci/ሚር. ኤሪክ ጌርሲ
ተማሪ አባል


## የት/ቤት አስተዳደር


Jack R. Smith, Ph.D.
የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

Maria V. Navarro, Ed.D.
የአካዴሚ ዋና መኮነን

Kimberly A. Statham, Ph.D.
የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ

Andrew M. Zuckerman, Ed.D.
አንድሩ ኤም. ዙከርማን
ዋና የኦፕሬሽን መኮንን



850 Hungerford Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
MARYLAND

የተከበራችሁ ጓዶች

በMontgomery County Public Schools (MCPS) ውስጥ እጅጉን ከፍተኛ ለሆኑ ግብረገባዊ ስነምግባርና ባለሙያነት ቃል የገባ ልዩ የሰራተኛ ሀይል አለን። አብረን፣ ለተማሪዎቻችን ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ትምህርቶችና አገልግሎቶች መስጠታችንን እና ከምረቃ በኋላ እነሱን ለስኬታማና ለአበልፃጊ ህይወቶች ማዘጋጀታችንን ለማረጋገጥ እንሰራለን። ይህ *የሰራተኛ ስነምግባር ኮድ* ለሰራተኞች በሞላ የተማሪዎቻችንን፣ የሰራተኛ ጓዶቻችን እና የሰፊው ማህበረሰብን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ አብረን እንዴት እንደምንሰራ MCPS የሚጠብቅባቸውን ግልፅ ለማድረግ ነው የቀረበው።

*የሰራተኛ ስነምግባር ኮድ* ለ2015–2016 የትምህርት አመት የዳበረ አዲስ ተነሳሽነት ነው። የሰራተኛ ስልጠና አካል በማድረግ ለዚህ ሰነድ መግቢያ ጨምረን ያለፈውን አመት በሙሉ ትግባሬውን ተቆጣጠርን። የሰራተኛ አባሎች *የሰራተኛ ስነምግባር ኮድ* የስራ ቦታዎቻቸው ጠቃሚ መገልገያዎች እንደሆኑ አስታውቀዋል። ከአስተያየቶች በመነሳት፣ በርካታ መሻሺያዎች ለ2016–2017 ትምህርት አመት አድርገናል። ለምሳሌ፣ በቅርብ ጊዜ የገቡ የMCPS ደንቦች ማጣቀሻዎች ጨምረናል። መጀመርያ፣ የMCPS ደንብ ACH-RA፣ *የስራ ቦታ ማሸማቀቅ*፣ የMontgomery County የትምህርት ቦርድ መመርያ ACH፣ *የስራ ቦታ ማሸማቀቅን* ለመተግበር ቅደም ተከተሎችን ያስቀምጣል። ሁለተኛ፣ የMCPS ደንብ GCC-RA፣ *የሰራተኛ መታሰር፣ የወንጀለኛ ክሶች፣ እና ፍርዶች በሰራተኛ በግል አመዘጋገብ*፣ ሁሉም ሰራትኞች በዚህ ደንብ በተዘረዘሩ የሆኑ ጥሰቶች ከታሰሩ ወይም ወንጀል ከተከሰሱ በራሳቸው ዘገባ ማድረግ አለባቸው። ይህ ግዴታ ሰላማዊ የመማርያ አካባቢ ለማቅረብ የMCPSን ግዴታ መግባት ያንጸባርቃል።

*የሰራተኛ ስነምግባር ኮድ* MCPS እና ሰፊው ማህበረሰብ፣ ሰራተኞቻችን በት/ቤታችን ስርአት ውስጥ ሚናዎቻቸውን ሲያካሂዱ፣ የሚጠብቁባቸውን የስነምግባር መመዘኛዎች ማጠቃለያ ነው። በተጨማሪ፣ የሰራተኛ ስነምግባር ኮድ፣ ሰራተኞች MCPS የሚጠቅባቸውን የማሟላት ተስእኖ ሁኔታዎችን ምላሽ ለመስጠት ጥቅም ላይ የሚውሉትን የዲሲፕሊን ቅደም ተከተሎች ያጠቃልላል።

ይህ ሰነድ እሴቶቻችንን ማንፀባረቁን፣ በስራ ቦታዎቻችን በሞላ ለመከባበር ባህል አስተዋፅኦ ማድረጉን ፣ እና ከሰራተኞች ያለንን ከፍተኛ ተጠባቂዎች በግልፅ ማስቀመጡን ለማረጋገጥ ከሰራተኛ ማህበሮቻችን፣ ሰራተኞች፣ እና ባለጉዳዮች ጋር አብረን መስራታችንን እንቅፅላለን። ለMCPS ተማሪዎቻችንና ቤተሰቦች በሞላ ለምታደርጉት ፅኑ አገልግሎት እናመሰግናለን።

ከማክበር ሰላምታም ጋር

Jack R. Smith, Ph.D.
Superintendent of Schools

## መግቢያ

Montgomery County Public Schools (MCPS) ለትምህርት፣ ግንኙነቶች፣ ልቀት፣ እና ለርትአዊነት ዋነኛ እሴቶቻችንን ለሚያራምድ ድርጅታዊ ባህል ግዴታ ገብቷል። ሁሉም ሰራተኞች ደህናና ጤናማ የትምህርት አካባቢዎች ለሁሉም ተማሪዎቻችን ለመፍጠርና ለመንከባከብ የተቻላቸውን ሁሉ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ሁሉም ሰራተኞች ከሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ በሁሉም ደረጃ ከሚገኙ ጓዶች፣ እና ማህበረሰብ ጋር እጅጉን ከፍ ባለ ሀቀኛነትና ባለሞያዊነት/professionalism እንዲገናኙ ይጠበቅባቸዋል።

ይህ *የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ* ሰራተኞች የዲስትሪክታቸውን ተልእኮ አስፈላጊውን ክፍል ሲያከናውኑ እንዲከተሉ MCPS እና ሰፊው ህብረተሰብ የሚጠብቅባቸውን ህጋዊ ተፈላጊዎችና መመዘኛዎች አጠቃላይ ማጠቃለያ ያቀርባል። በተጨማሪ፣ የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ ሰራተኞች የሚፈለጉባቸውንና የስነ ምግባር መመዘኛዎችን ማሟላት ሲሳናቸው ሁኔታዎችን ለማስተካከል MCPS የሚጠቀምባቸውን የዲሲፕሊን ቅደም ተከተሎችን ያጠቃልላል።

የስነምግባር ኮድ በሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ የምስክር ወረቀት ያላቸውንና የሌላቸውን ሁለቱንም፣ ቋዋሚና ከፊል-ጊዜ፣ እንዲሁም ተተኪዎችና በጊዜያዊነት ወይም ለወራት የተቀጠሩ ሌሎች ላይ ተግባራዊነት አለው። የስነምግባር ኮድ በርካታ ገፅታዎች የተመሰረቱት በMontgomery County የትምህርት ቦርድ መመርያዎችና በMCPS ደንቦችነ ሊሎች መመርያዎች (ከዚህ በኋላ የMCPS ህጎች ርሚባሉ)፣ አንዲሁም በድርድር ስምምነቶችና በስቴትና በፌደራል ህጎች ላይ ነው። ይህ የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ አነዚህን መገልገያዎች እንዲተካ አልታሰበም፣ ይልቁንስ ለሁሉም ሰራተኞች ጠቃሚ የሚሆን የአንድ-ሰነድ ማጠቃለያ እና አግባብነት ያላቸው ነገሮች መጣቀሻ ምእራፍ ለማቅረብ እንጂ። እባካችሁ አስተውሉ ይህ የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ ኮንትራት አይደለም፣ እናም የሚጠቅሳቸው መመርያና ህጋዊ ግዴታዎች ሊለወጡ የሚችሉ ናቸው በዚህ ህትመት በሚገኙት አረፍተሀሳቦችም ላይ የበላይነት አላቸው።[1]

# የሰራተኛ ስነምግባር ግዴታዎች

MCPS ሁሉም ሰራተኞች ስራቸውን በተፈላጊ ክሂሎትና እውቀት እንዲፈፅሙ፤ እጅግ ከፍተኛ የሃለፊነትና የግብረገባዊ ስነምግባር ደረጃ እንዲንከባከቡ፤ እና አግባብ ያላቸውን ሁሉንም ህጎች፣ መመርያዎች፣ እና ደንቦች እንዲያከብሩ ይጠብቃል። የሆነ ሰራተኛ በሚቀጥሉት እንቅስቃሴዎች ወይም ስነመግባር በምንም አይነት መሳተፍ የለበትም፡- ያካሄድ ጥፋት፣ በቢሮ መጥፎ አመል (የተጠረጠረ የልጅ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኛነትን አውቆ አለማስታወቅን የሚያካትት)፣ አለመታዘዝ፣ ድክመት፣ ወይም ሆን ብሎ ስራን ቸል ማለት።

ሰራተኞች ስነምግባቸውን የሚመለከት ግብረ-ገባዊ ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይ ባጋጠማቸው ማንኛውም ጊዜ፣ MCPS አንድን ህግ፣ መመርያ፣ ደንብ፣ ወይም ያንድ ሀላፊነትና ግብረ-ገባዊ ስነምግባር ስሜት ሙያዊ መመዘኛ ተጥሶ እንደሆነ እንዲያገናዝቡ ይጠብቅባቸዋል። በዚያው መጠን አስፈላጊ፣ ሰራተኞች የሚከተለውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ ወይም ስነርምግባር ከሚያስከትል መቆጠብ አለባቸው፡-

- የተማሪዎችን፣ የስራ ጓደኞችን፣ ወይም የሰፊው ማህበረሰብን ደህንነት የሚያሰጋ
- የሰራተኛው(ዋ)ን ባለሙያዊ ሀቀኛነት የሚያዳክም፤ እና/ወይም
- የተመደቡላቸውን ስራዎች ለመፈፀም ብቁ እንዳይሆኑ የሚያደርጋቸው።

በሚከተሉት ገፆች የሚገኙት ሰንጠረዦች MCPS ከሰራተኞቹ በሞላ የሚጠብቀውን የስነምግባር ደረጃዎች ናሙናዎች፣ እንዲሁም እርማት ወይም የዲሲፕሊን እርምጃ የሚጠይቅ ስነስርአት የጎደለው ወይም ረብሸኛ ስነምግባር ያቀርባሉ። የአንድ/ዲት ሰራተኛ የሚጠበቅበ(ባ)ትን ስነምግባር መፈፀም አለመቻል፣ እንዲሁም የሰራተኛው ስነስርአት የጎደለው ስነምግባር መፈፀም (በሚቀጥሉት ገፆች የተዘረዘሩትን "መደረግ የሌለባቸው"ን ጨምሮ፣ ግን በነሱ ያልተወሰኑ)፣ እስከ መታገድ ወይም መሰናበት የሚያካትት፣ የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲወሰድበት ሊያደርሰው ይችላል።

ሁሉም ስነስርአት የጎደለው፣ ተገቢ ያልሆነ፣ ወይም ግብረገብ የጎደለው ስነማግባር በሞላ በዚህ ህትመት በግልፅ ሊጠቀስ እንደማይችል ሰራተኞች መገንዘብ አለባቸው። ይልቁንስ፣ በሚቀጥሉት ገፆች የሚገኙት ናሙናዎች ስእላዊ/መግለጫና ሁሉንም የማያካትቱ ናቸው። በግልፅ ያልተዘረዘረ ስነምግባር እንዲያውም የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስከትል ይችላል። ለምሳሌ፣ ሰንጠረዦቹ በዘልምድ አስተሳሰብ ወይም በጋራ ግንዛቤ ቀና ልምዶች የተመሰረቱ የሰራተኛ ስነ ምግባሮችን እያንዳንዳቸውን ለመዘረዘር አይሞክሩም።

## 1. ግብረገባዊ ስነምግባር በስራ አካባቢ

ሰርተኞች ታማኝ እንዲሆኑ፣ በርትተው የስራ ሀላፊነቶቻቸውን እንዲያሟሉ፤ ሁሉንም ህጎች የMCPS ደንቦች፣ እና ስራቸውን የሚገዙ ስነምግባራዊ መመዘኛዎች እንዲያከብሩ፤ እናም ይህን አለመፍፀም ከስራ ውጭ ተግባራቸውን ለመፈጸም ብቃታቸው ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ከሆነ ህጎችንና የMCPS ደንቦችን ማክበር።

የሚጠበቅ ስነምግባር ምርጥ ምሳሌዎች፡-

- የስራ ትእዛዞችን በተገቢ፣ አጥጋቢ፣ እና ወቅታዊ መንገድ ማሟላት እና የMCPS፣ የመምርያ፣ እና የት/ቤት ሂደቶችና መመርያዎች፣ እንዲሁም የተቆጣጣሪዎችና የአስተዳዳሪዎችን ትምህርቶች፣ አመራሮች፣ እና ትእዛዞች መከታተል።
- ለስራ በፕሮግራም መሰረት መድረስ፣ እስከተጠበቀው ድረስ መስራት፣ የስራ ፈቃድ ሂደቶችን ማክበር፣ እና የስራን ጊዜ ለMCPS ሀላፊነቶች አፈፃፀም መገልገል።
- ለስራ አግባብ ባለው ሙያዊ መልክ መልበስ።
- የህግ ግዴታዎችንና የMCPS ደንቦችን ስለ ግብረ-ገባዊ ስነምግባር አክብሩ የጥቅም ግጭቶችንም አስወግዱ።[2]
- በስራ አማካይነት የምታገኙት መረጃን፣ የሰራተኛና የተማሪ ዘገባዎችን ጨምሮ፣ ምስጢራዊነት መንከባከብ።[3]
- ስለ MCPS ወጪዎችን ሲያደርጉ መጠንቀቅና ማስተዋል እናም ከMCPS ኦፊስየል ቢዝነስ ጋር በቀጥታ ለተያያዙ ውጭዎች መተኪያ ማንኛቸውም ጥያቄዎች ሲያቀርቡ ሁሉንም ተፈላጊዎች/ግዴታዎች ማክበር።[4]
- ሁሉንም ተፈላጊ ዘገባዎች በወቅቱ ማከናወን እና ፕሮግራምንና የፋይናንስ ዘገባ አቀራረብ መመርያዎችን መከተል።
- ሁሉንም ተፈላጊ የMCPS ሞያዊ የትምህርት እድሎች ሙሉ በሙሉ መከታተልና መሳተፍ፣ እናም የተመደቡበትን የMCPS ቦታ ለመያዝ የሚያስፈልገውን ዋጋ ያለው ሰርቲፊኬት/certification/licensure በሚገባ ለመጠበቅ ሁሉንም የኮርስ ስራና ስልጠና መፈፀም።
- በተግባራዊው የሙያ እድገት ስርአት/Professional Growth System ውስጥ ያሚገኙ መስፈርቶችን ማንበብና ማክበር።
- የታወቁ ወይም የተጠረጠሩ የማጭበርበር፣ የውሸት ይገባኛሎች፣ የውሸት አረፍተሀሳቦች፣ ጉቦ፣ ሌብነት፣ ወይም የMCPS ገንዘቦች ወይም ንብረት ሙስና/ አደራ መብላት ሁኔታዎች ዘገባ ማቅረብ።
- ለMCPS ገንዘቦች ፋይናንሳዊ ሀላፊነት መተግበርና በሚገባ ሂሳብ መያዝ፣ የMCPSን ንብረት መጠበቅ፣ እና የሌሎችን ንብረት ማክበር።
- በአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና በሌሎች እፆች[6] በMCPS ንብረት አጠቃቀምን የሚከለክሉ ህጎችንንና የMCPS ደንቦችን ማክበር።[7]
- የት/ቤትን ደህነትና ፀጥታ የሚመለከት ህጋዊ ግዴታዎችንና የMCPS ህጎችን መከታተል/ማክበር።

- በMCPS ድርጣብያዎች፣ ኢሜይል፣ እና በሌሎች የመገናኛ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በሚመለከት ህጋዊ ግዴታዎችንና የMCPS ህጎችን መከታተል/ማክበር፣[8] እንዲሁም የደህንነትንና የመረጃ ምዝገባ ግዴታዎችን መፈተን።[9]
- አስፈልጊ ሲሆን በወንጀል መታሰሮችን፣ ክሶችን፣ ወይም ፍርዶችን በግል ዘገባ ማዘጋጀት።[10]
- በፖለቲካ ዘመቻዎች፣ የፓርቲ ምርጫ አንቅስቃሴዎች፣ እና በፖለቲካ ወይም በፓርቲ ቁሳቁሶች ስርጭት ተሳትፎ የMCPS ደንቦችንና የስቴት የምርጫ ህጎችን ማክበር።[11]
- በMCPS፣ የህግ አስከባሪ፣ ወይም በሌሎች የምርምራ ሀላፊነት ያላቸው መኮንኖች ለሚቀርብ ከስራ ጋር ለተያያዘ ጥያቄ በቀና መመለስ።
- ተማሪዎችን በሚያካትቱ በት/ቤት ስፖንሶር የሆኑ ጉዞዎችን በMCPS ደንቦችና አግባብ ባለው ፈቃድ ማካሄድ።[12]
- የግል ህይወት እንቅስቃሴዎችን (የማህበራዊ ሚድያ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ) የMCPS ሰራተኛን ውጤታማነት ጥያቄ ውስጥ በማያስገባ ሁኔታ መተግበር እና ወንጀለኛ፣ እምነተ ጎደሎ፣ እና ሌሎች ተገቢ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች ከMCPS ጋር ላለህ ቅጥርና ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያመጡ እንደሚችሉ መገንዘብ።[13]

ስርአት የጎደለው ስነምግባር ምርጥ ምሳሌዎች፡-

- የተማሪዎችን፣ ሰራተኞችን፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ወይም የህዝብን ደህንነት አደጋ ላይ በሚጥል ስነምግባር አትሳተፉ።
- ስራችሁን ጥላችሁ አትሂዱ።
- በአጭር የስራ ታሪካችሁ በስራ ማመልከቻችሁ የውሸት መረጃ አትስጡ ወይም ጉልህ/አስፈላጊ ነገር አትቀንሱ።
- ፈቃድን ለአግባብ አለመጠቀም ወይም ለመተኪያ ወጪ፣ ወይም ክፍያ፣ ሀሰተኛ ወይም የማጭበርበር ጥያቄ አለማቅረብ።
- ለMCPS ወይም ስለ MCPS የተሳሳተ ወይም የማጭበርበርያ ጥያቄ አታቅርቡ።
- አትስረቁ።
- የግል ጥቅም ባለዎት ማስኮች ለMCPS በሚሰሩበት ወቅት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ አትሳተፉ፣[14] ወይም የርስዎን ቦታ እንደ የMCPS ሰራተኛ፣ ወይም በመቀጠርዎ በሚያገኙት መረጃ፣ ለግል ጥቅም አያውሉት።
- ባለቤታችሁን፣ ዘመድ፣ አማች፣ ወይም የቅርብ ግላዊ ዝምድና ያላችሁን ሰራተኛ በስራ ገበታ አትቆጣጠሩ/አለቃው/ዋ ሆናችሁ አትስሩ።
- በMCPS ደንቦች ካልተፈቀዱ በስተቀር ስጦታዎች አለመቀበል።[15]
- በMCPS መመርያ ወይም ደንብ ካልተፈቀደ በስተቀር የግል አስተማሪነት ስራ ከትምህርት ሰአት-በፊት፣ ከትምህርት ሰአት-በኋላ፣ ወይም በሰመር እንቅስቃሴዎች ለክፍያ አትስጡ/አታከናውኑ።[16]
- በMCPS ንብረት ላይ ወይም MCPS ስፖንሰር በሚያደርገው እንቅስቃሴ ጠመንጃዎች ወይም ሌሎች የጦር መሳርያዎች አትያዙ።[17]

## 2. ገብረገባዊ ስነምግባር ከተማሪዎች ጋር

**የሙያዊ ልምዶች መስፈርቶችን እየጠበቁ፣ ሁሉም ሰራተኞች ትምህርትን ለመደገፍ ከተማሪዎች ጋር አወንታዊ ግንኙነቶችን እንዲገነቡ ይጠበቃል።**

### የሚጠበቅ ስነምግባር ምርጥ ምሳሌዎች፡-

- ሁሉንም ተማሪዎች ያለ አድልዎ፣ በርትይአዊነት፣ እና በአክብሮት መያዝ ዘር፣ ቀለም፣ ትውልድ፣ ብሄራዊ ምንጭ፣ ሀይማኖት፣ ፆታ፣ የፆታ ምንነት፣ የፆታ አዝማምያ፣ እድሜ፣ የጋብቻ ይዞታ፣ የቤተሰብ ይዞታ፣ማህበራ "ዊኤ" ኮኖሚያዊ ይዘት አካላዊ ጠባዮች፣ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ስንክልና፣ ወይም ሌላ በህግ የተጠበቀ ጠባይ የፈለገውን ይሁን።[18]
- ለሁሉም ተማሪዎች ተቀባይነት ያለው፣ የጠሩ፣ እና እድሜን ያገናዘቡ ከፍተኛ ተጠባቂዎች መጠበቅ።
- ደህናና አስተማማኝ አካባቢ እንዲኖር ለማድረግ የተማሪን ስነምግባርና አግባብ ያለው ምላሽ አሰጣጥ ስልቶች ለመምራት አግባብ ባለው የጣልቃገብነት ስልቶችና ድጋፍ መጠቀም።
- የተማሪን ግላዊ አካባቢ/space ማክበር።
- የልጆች ወይም የደካማ አዋቂዎችን ማጎሳቀልና ቸልተኝነት እንደታየ ወይም እንደተጠረጠረ ወድያውኑ ዘግባችሁ አሳውቁ እናም በማጎሳቀልና ቸልተኝነት ዘገባ ጣልቃ አትግቡ።[19]
- ከተማሪዎች ጋር የሚኖሩ የኢሜይልና የማህበራዊ ግንኙነቶችን ከማስተማርና ከMCPS ስራ ሀላፊነታችሁ በቀጥታ በተያያዙ ተገቢ አላማዎች ብቻ መቆጠብ።

### ስርአት የጎደለው ስነምግባር ምርጥ ምሳሌዎች፡-

- በዘር፣ ቀለም፣ ትውልድ፣ ብሄራዊ ምንጭ፣ ሀይማኖት፣ ፆታ፣ የፆታ ማንነት፣ የፆታ አዝማምያ፣ እድሜ፣ የጋብቻ ይዞታ፣ የቤተሰብ ይዞታ፣ማህበራ "ዊኤ" ኮኖሚያዊ ይዘት አካላዊ ጠባዮች፣ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ስንክልና፣ ወይም ሌላ በህግ በተጠበቀ ጠባይ በተማሪዎች ላይ አድልዎ አታድርጉ።
- ተማሪዎችን አታሸማቅቁ፣ አታዋክቡ ወይም አታስፈራሩ።[21]
- ማንኛውንም ልጅ ሆነ ደካማ ሽማግሌ ወይም የተማሪው/ዋ እድሜ የፈለገውን ይሁን፣ ከአንድ የMCPS ተማሪ ጋር የፍቅር ወይም የፆታ ግንኙነት ለማድረግ አትሳተፉ ወይም አትሞክሩ።
- ከአንድ ተማሪ ጋር አንድ-ለአንድ በተዘጋ ወይም መብራቶቹ በጠፉ አንድ ክፍል ውስጥ አትገናኙ።
- ወሲብ-ነክ ፅሁፍ/ቪድዮ ለMCPS ተማሪዎች አታሳዩ፣ ወይም ልጆችን ከወሲብ-ነክ ሁኔታ ጋር አታገናኙ/አታሳትፉ።
- በማንኛውም የMCPS ንብረት ወይም በማንኛውም የMCPS እንቅስቃሴ ወሲብ-ነክ ነገር አታስታዋውቁ ወይም አታሳዩ።

- ተገቢ ባልሆኑ አካላዊ ግንኙነቶች ከተማሪዎች ጋር አትሳተፉ፣ ለምሳሌ—
    - መምታት፣ ማሳሳቅ፣ ወይም መሳም፤
    - የተማሪን የሆነ አካል መዳሰስ፤
    - ለልጅ ወይም በልጅ የሚደረግ የአካል መታሸት፤ እና
    - የፆታዊ ትርጉም ያላቸው ጎጂ ስእሎች፣ ማስታወሻዎች፣ ክርቱኖች፣ ወይም ቀልዶች መላክ።

    *ማሳሰቢያ፡- አንዳንድ መነካካቶች በተወሰኑ ሁኔታዎች አግባብነት ሊኖራቸው ይችላል፣ ለምሳሌ ቀላል መታ መታ በጀርባ ወይም ትከሻ ላይ፣ በእጅ መጨባበጥ፣ አምስቶች/high fives፣ ወይም አነስተኛ ልጆችን በእጅ ይዞ መምራት።*

- ከተማሪዎች ጋር ተገቢ ያልሆነ የቃል ልውውጥ አታድርጉ፣ ለምሳሌ—
    - ስድብ ወይም ፀያፍ አነጋገር፤
    - ያንድን የግል ህይወት ምስጢራዊ ዝርዝሮች መወያየት፤
    - ተማሪዎችን ምስጢሮችን ለአዋቂዎች እንዳይገልፁ ማደፋፈር፤
    - ፆታዊ ወይም ጎጂ ቀልድ፤
    - ማሳፈር፣ ማንቋሸሽ፣ ወይ የሚያዋርዱ መልእክቶች ስለ አንድ ተማሪ፣ ስለተማሪው አካል፣ የአካል እድገት፣ አለባበስ፣ ወይም ቤተሰብን ጨምሮ፣ አሉታዊ አስተያየቶች መሰንዘር፣ እና
    - ልጆችን ሊያስፈራ፣ ሊያንቋሽሽ፣ ወይም ሊያሳፍር የሚችል መጥፎ/አስከፊ ቋንቋ።
- ከMCPS ተማሪዎች ጋር በማህበራዊ ሚድያ፣ ኢሜይል፣ ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ከትምህርት ወይም የMCPS የስራ ድርሻችሁ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ከሌለው በስተቀር አንድ-ለአንድ ግንኙነት አታድርጉ።
- ከተማሪዎች ጋር ለመገናኘት ወይም "ጓደኞች" ለመሆን በግል ኢሜይል ሂሳቦች፣ የማህበራዊ ሚድያ ጣብያዎች፣ ወይም ሌላ ኤሌክትሮኒክ መገናኛዎች አትጠቀሙ።
- ያለ ወላጅ/አሳዳጊ እና የት/ቤት አስተዳዳሪ ፈቃድ ውጭ አንድን ተማሪ በግል መኪና አታሳፍሩ፣ እና፣ ከተቻለ፣ አሽከርካሪውንና ተማሪውን ሁለተኛ አዋቂ እንዲያጅባቸው አድርጉ።
- አስተዳዳሪ አስቀድሞ ካልፈቀደ በስተቀር ለግል ተማሪ ስጦታዎች አትስጡ።
- የአካል ቅጣት/ግርፍያ ወይም ሌላ ተገቢ ያልሆኑ ማንቀጥቀጥ/ማወዛወዝ፣ በጥፊ ማጮል፣ መግፋት፣ መቆንጠጥ፣ ማባረር፣ ወይም የሚበላ፣ የሚጠጣ፣ ወይም ህክምና መከልከልን በማሳሰሉ የዲሲፕሊን ልምዶች አትገልገሉ።[23]
- በተወሰኑ በMCPS ደንቦችና ብዲስትርክት ስፖንሶር በሆነ ስልጥናና መመርያ ከተቀመጡ ሁኔታዎች በስተቀር፣ በአካላዊ ማገቻ ፣ ወይም በተማሪዎች መገለል አትጠቀሙ።

## 3. ግብረገባዊ ስነምግባር ከጓዶች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ማህበረሰብ ጋር

ሰራተኞች ወላጆችን/አሳዳጊዎችን፣ ሌሎች ሰራተኞችን፣ እና የማህበረሰብ አባላትን በባለሙያዊነት/professionally እና በአክብሮት እንዲይዙ እና ከሌሎች አዋቂዎች ጋር ባላቸው ግንኙነቶች ሁሉንም ፀረ-አድልዎ ሕጎችንና መመርያዎች እንዲያከብሩ ይጠበቅባቸዋል። ሁሉም ሰራተኞች ስለሌሎች ግለሰቦች ጥቅሞች፣ አስታያየቶች፣ ባህሎች፣ እና ያለፈ ታሪክ ንቃት፣ ግንዛቤ እና ቻይነት እንዲኖራቸው ያንኑ ያህል ወሳኝ ነው።

የሚጠበቅ ስነምግባር ምርጥ ምሳሌዎች፡-

- በሁሉም ግንኙነቶች ትሁት መሆን እና የሌሎችን አስተያየቶች መፈለግና ማክበር።
- ለወላጆች/አሳዳጊዎችና ለት/ቤት ማህበረሰብ የሚጋብዝ/የሚስብ አካባቢ መፍጠር።[25]
- በግልፅነትና በመከባበር መገናኘት።
- ከስልጣን ቦታና ከአንፃራዊ ኣቀራረብ ይልቅ በትግብብሮሽና በጥቅም/ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ስልቶች መጠቀም።
- አስተያየቶችን በገንቢ አቋምና በመከባበር ማቅረብና መቀበል።
- በMCPS ንብረት ላይ ለጎብኝዎች፣ በጎ-ፈቃደኞች፣ እና ስራ ተቋራጮች ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ።[26]
- የሌሎች ሰራተኞች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና ሌሎች በት/ቤቱ ማህበረሰብ የተለያዩ አስተያየቶችና እምነቶችን ማክበር

ስርአት የጎደለው ስነምግባር ምርጥ ምሳሌዎች፡-

- በሌሎች ላይ ብልግናና ወራዳ ስነምግባር አታሳዩ።
- በዘር፣ ቀለም፣ ጎሳ፣ ብሄራዊ ትውልድ፣ ሀይማኖት፣ ፆታ፣ የፆታ ማንነት፣ የፆታ አዝማምያ፣ እድሜ፣ የጋብቻ ይዞታ፣ የቤተሰብ ይዞታ፣ የማህበራዊ-ኤኮኖሚያዊ ይዘት፣ አካላዊ ጠባዮች፣ አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ስንክልና፣ ወይም ሌላ በህግ በተጠበቀ ተግባራዊ ህግ መሰረት ወላጆች/አስዳጊዎች፣ የስራ ጓዶች፣ ተቆጣጣሪዎች ወይም ሌሎች ዜጎች ላይ አድልዎ አትፈፅሙ።[27]
- የMCPSን ሰራተኞች ወይም ሌሎች አዋቂዎችን አትበድሉ፣ አታዋክቡ፣ ወይም አታስፈራሩ።[28]
- አንድ እርምጃ በመውሰዱ/ዷ፣ ወይም ስለ ማናቸውም ሁኔታዎች ወይም የሆኑ ወይም የታለሙ መጥፎ ተግባሮችን የሚመለከት መረጃ ዘገባ በማቅረቡ/ቧ በሰራተኛ ወይም ሌላ ግለሰብ ላይ አፀፋ አትውሰዱ።

## የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ ትግባሬና አፈፃፀም

ይህ የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ የታሰበው የMCPS ሰራተኞች ስነምግባርን በሚመለከት ተጠባቂዎችን/ግዴታዎችን የሚገዙ የተለያዩ ህጋዊና ሌሎች ግዴታዎችን ለማወሀሀድና ተጨማሪ ድህረእይታ ለማቅረብ ነው። እነዚህ በንዚህ ብቻ ባይወሰኑም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

1. Education Article of the Annotated Code of Maryland እና Code of Maryland Regulations (COMAR) የመምህራንን፣ ርእሰመምህራንን፣ ረዳት መምህራንን፣ እና ሌሎች የስራ መደባቸው በMaryland State Department of Education ሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ (MSDE) የተሰጠ የባለሙያ የምስክር ወረቀት የሚጠይቅ የህዝባዊ ት/ቤት ሰራተኞችን በሚመለከት ያስቀመጧቸው ግዴታዎች[29] እናም እነዚያ የምስክር ወረቀት ያላቸው ሰራተኞች እነዚህን መስፈርቶች ማሟላት ሲሳናቸው የእገዳና የስንብት እርምጃዎች መስፈርቶች ማቅረብ። በተጨማሪ፣ የት/ቤት ተሽከርካሪ አንቀሳቃሾችና ረዳቶች አንዳንድ ግዴታዎችን ማሟላት ሲሳናቸው፣ የስቴት ህግ ከማሽከርከር እና/ወይም ከቅጥር ሊከለክላቸው ይችላል።[30]

2. ሌሎች ፌደራላዊና የስቴት ህጎች ለMCPS ሰራተኞች የሌላ ግለሰብን ሰውነት፣ ንብረት ወይም ዝና ደህንነት፣ ፋይናንሳዊና ፕሮግራም ተጠያቂነት፣ የልጅ ማጎሳቆልና ችልተኝነት፣ የተማሪና የፔርሶኔል ዘገባዎች፣ እና ሰብአዊ መብቶችና ፀረ አድልዎ ግዴታዎችን በሚመለከት ግዴታዎችን መስርቷል።

3. ከMontgomery County Education Association/የትምህርት ማህበር (MCEA)፣ Service Employees International Union Local 500/ የአገልግሎት ሰራተኞች አለምአቀፍ አንድነት ማህበር Local 500 (SEIU) እና የMontgomery County Association of Administrators and Principals/Business and Operations Administrators/ የአስተዳዳሪዎችና ርእሰመምህራን/ቢዝነስና እና የኦፔሬሽን አስተዳዳሪዎች (MCAAP/MCBOA) ጋር በድርድር የተፈጠሩ የህብረት ስምምነቶ ችየሰራተኛን ስነምግባር የሚመለከቱ ግዴታዎች፣ የሰራተኛ የህጋዊ ሂደት መብቶች፣ እና MCPS በ"በቂ መነሾ" በሰራተኞች የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ እንደሚችል እውቅና የሚሰጡትን አስቀምጠዋል።[31] ይህ ስነስርአት ሰራተኞች የስነምግባር ደረጃዎችን ማክበር እንዳለባቸው እና ይህን አለማሟላት ለዲሲፕሊን እርምጃ ወይም ከስራ ስንብት "በቂ መነሾ" ሊሆን እንደሚችል እውቅና ይሰጣል።

4. በMCPS፣ MCEA፣ MCAAP፣ እና በSEIU መካከል የተገባው Culture of Respect Compact/የመከባበር ባህል አንድነት የያንዳንዱን ሰራተኛ ስኬት፣ ከፍተኛ የተማሪ ግኝት፣ እና ራሱን በሚያድስ ድርጅት ቀጣይ

መሻሻል ለማረጋገጥ አወንታዊ የስራ አካባቢ ለማራመድ ለMCPS ሰራተኞች ተጠባቂዎችን/ግዴታዎችን ያስቀምጣል።[32]

5. የሞያዊ እድገት ስርአቶች/Professional Growth Systems ለሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ በያንዳንዱ የህብረት ስምምነት እንደተሰጡት፣ የሚጠበቁትን የስራ አፈፃፀም መስፈርቶች በከፍተኛ ዝርዝር ይለያሉ፣ እነዚያን ግዴታዎች የሚያሟላና የማያሟላ የስነምግባር በርካታ ምሳሌዎች እየሰጡ። የሞያዊ እድገት ስርአቶች እነዚያ ግዴታዎች መከበራቸው ለማረጋገጥ የታሰቡ የግምገማ መሳርያዎችም በተጨማሪ ይገልፃሉ።[33]

6. የቦርድ መመርያዎች እና የMCPS ደንቦች ግብረገብ፣ ፋይናንሳዊ አስተዳደር፣ የልጅ ማዋከብና ቸልተኝነት፣ እና አድልዎ አለማድረግን ይገዛሉ እናም ስነምግባርን በሚመለከት ግዴታዊነቶችን ይፈጥራሉ።[34] በተጨማሪ፣ የትራንስፖርት መምርያ Just Cause Standards for Bus Attendants and Bus Operators/ለአውቶቡስ ረዳቶችና አውቶቡስ ነጂዎች ትክክለኛ መመዘኛዎች የሚል የሰራተኛ የመመርያ ምፅሀ ፍአለው።[35]

ስነምግባራቸው እነዚህን የተለያዩ ደንቦች/ደረጃዎች ማክበር የሁሉም የMCPS ሰራተኞች ሀላፊነት ነው። ይህን አለማድረግ፣ በህብረት ስምምነቶች በታቀፉት የሰራተኛ ዲሲፕሊን ደንቦች፣ በProfessional Growth System/የሞያዊ እድገት ስርአት በሚገኙት የመሻሻል ሂደት፣ ወይም፣ የምስክር ወረቀት ላላቸው ሰራተኞች፣ በEducation Article of the Annotated Code of Maryland/በሜሪላንድ የትምህርት አንቀፅ ኮድ በክፍል 6-202 መሰረት በእገዳና በስንብት ሂደቶች፣ በየሁኔታው እንደአግባቡ የመጠቀም ውጤት ሊያደርስ ይችላል። በተወሰኑ ሁኔታዎች፣ ከአንድ አቀራረብ በላይ ተገቢ ሊሆን ይችላል። በህግ፣ በቦርድ መመርያዎችና በMCPS ደንቦች፣ እና በህብረት ስምምነቶች መሰረት በተያዙት የቅሬታና የይግባኝ ቅደም ተከተሎች ድህረእይታና ይግባኝ የተጠበቁ ሆነው፣ እንደነዚህ አይነት እርምጃዎች እንደ እያንዳንዱ ጉዳይ መሰረት በMCPS ተጀምረው ይወሰናሉ። ይህ የስነምግባር ኮድ አንድን ሰራተኛ የዲሲፕሊን ተገዥ ሲያደርጉት፣ አንዳንድ ሁኔታዎች በProfessional Growth System/ሞያዊ እድገት ስርአት አማካይነት ሊያዙ ይቻላል ወይም ይገባል።

## ማረሚያና ተራማጅ ዲሲፕሊን

MCPS ሰራተኞቹን ማረሚያና ተራማጅ - ሁለቱንም - በያዘ የዲሲፕሊን ሂደት በርትአዊነትና በፅኑ መንገድ ለመያዝ ግዴታ ገብቷል።

1. ዲሲፕሊን ያልሆኑ ማረሚያ እርምጃዎች በተወሰኑ ሁኔታዎች፣ አንድ ተቆጣጣሪ ወይም ስራ አስኪያጅ የአንድ ሰራተኛ ስነምግባር ኦፊሴላዊ

የዲሲኦፕሊን እርምጃ አያስፈልገው(ጋት)ም ነገር ግን የወደፊቱ(ቷ)ን ስነምግባር በሚመለከት ስለ ግዴታዎች ማብራርያ ያስፈልገዋ(ጋታ)ል ብሎ መወሰን ይችላል። በእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ፣ ተቆጣጣሪው ወይም ስራ አስኪያጁ የሚጠበቀውን የወደፊቱን ስነምግባር በሚመለከት የጽሁፍ መመሪያ ሊሰጥ ይችላል። የዚህ አይነቱ ሰነድ የዲሲፕሊንነት ጠባይ አለው አይባልም፣ ነገር ግን በምስጢራዊነት ዘገባ ይያዛል ምክንያቱም የሰራተኛው ስነምግባር የተላለፈለትን ግዴታዎች የማያከብር ከሆነ ለወደፊት የዲሲፕሊን እርምጃ ድህረአይታ ማቅረብ ስለሚችል።

2. የዲሲፕሊን እርምጃዎች። የዘልምድ የዲሲፕሊን እርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ
- የፅሁፍ ነቀፌታ
- እገዳ ያለደሞዝ
- ከስራ ደረጃ መውረድ
- ከስራ ቦታ መወገድ/መነሳት
- ስንብት

MCPS ምንም በተወሰነ የተራማጅ ዲሲፕሊን ደረጃ የመጠቀም ወይም እላይ በተዘረዘረው ደረጃ መሰረት በእርምጃዎች የመጠቀም ግዴታ የለበትም። ይልቁንስ፣ የያንዳንዱ ሁኔታ ልዩ ሀቆች ከተዘረዘሩት የዲሲፕሊን እርምጃዎች የትኛው ተገቢ እንደሚሆን ይወስናሉ። በያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢው የዲሲፕሊን እርምጃ ደርጃ ውሳኔ ሲደረግ፣ ማሻሻያ ታሳቢዎች (ለምሳሌ የሰራተኛው ረዥም የጥሩ አገልግሎት ታሪክ ከንፁህ ዘገባ/ሪኮርድ ጋር ወይም በሰራተኛው በኩል አነስ ያለ ጥፋተኛነት) ወይም ማባባሻ ታሳቢዎች (ለምሳሌ ሌሎችን ለፅኑ ጉዳት አደጋ መዳረግ፣ ሆነ ብሎ መጥፎ ድርጊት ማሳየት፣ ወይም አንድ ድርጊት በሌሎች ላይ ሊያደርስ ስለሚችለው ውጤት ግድየለሽነት) ሊገናዘቡ ይችላሉ። ይህን የስነምግባር ደንብ፣ ወይም ተገቢ መመርያዎችና ደንቦች፣ ግንዛቤ አለመኖር ወይም አለማወቅ፣ ለጥፋት ክስ መከላከያ አይደለም።

ለከፍተኛ ጥሰቶች ካልሆነ በስተቀር፣ በሚቀጥሉት ገፆች የሰፈሩትን የተከለከሉ የወንጀለኛ ስነምግባሮች ነገር ግን በነሱ ያልተወሰነን ጭምሮ፣ የሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ደረጃ መተግበር ያለበት በቅድሚያ ሰራተኛው ግዴታዎችን እንዲገነዘብና ተገቢ ያልሆነውን ስነምግባር እንዳይደግም ለማረጋገጥ ላይ ማተኮር አለበት። ባጠቃላይ፣ ዲሲፕሊን ወደ ከባድ ደረጃ ማደግ ያለበት ዝቅተኛ የዲሲፕሊን እርምጃ ተተግብሮ ውጤትየለሽ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ነው። ቢሆንም፣ እንደየሁኔታው፣ ለመጀመርያ ጥፋትም ይሁን፣ ወይም ለተደጋጋሚ ጥፋቶች፣ የበለጠ ከባድ ጥሰት መታገድ ወይም ስንብት

ሊያስከትል ይችላል። ይህም ጥሰቱ ተለይቶ በፅሁፍ የተቆጠረ ባይሆንም ነገር ግን የገዢ መርህዎች ወይም የወንጀለኛ መቅጫ ህግ የተፈጥሮ አስተሳሰብ ትግባሬ ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው።

3. የልጅ ማጎሳቆልና ሌላ የወንጀል ትግባሬ የሚያካትቱ ጉዳዮች ሂደት። በMCPS ሰራተኛ የልጅ ማጎሳቆልና ወይም ቸልተኝነት ጥርጣሬ የሚያካትቱ ጉዳዮች በስቴት ህግ፣ በቦርድ መመርያ JHC፣ እና በMCPS ደንብ JHC-RA በሚጠይቁት መሰረት በMontgomery County Department of Health and Human Services/በጤናና ሰብአዊ አገልግሎቶች ለChild Welfare Services፣ በይፋ Child Protective Services/የልጅ ጥበቃ አገልግሎቶች (CPS) ተብሎ ለሚታወቀው፣ እና፣ የፆታ ማጎሳቆል ጉዳይ ከሆነ፣ በMontgomery County Police Department/የፖሊስ መምርያ (MCPD) ለSpecial Victims Investigations Division/የልዩ ምርመራ ክፍል በተጨማሪ ወድያውኑ የቃል ዘገባ ያስፈልጋል። በማንኛውም የተጠረጠረ ማጎሳቆል ወይም ቸለተኝነት በMCPS ሰራተኛ፣ Office of Human Resources and Development/የሰው ሀይልና እድገት ፅ/ቤት (OHRD) በተግባር ላይ በሚገኙት የቦርድ መመርያዎችና የMCPS ደንቦች መሰረት የውስጥ ምርመራ አካሂዶ ተገቢ የዲሲፕሊን ሀሳብ ያቀርባል። ምንም እንኳን CPS ወይም MCPD እርምጃ ሳይወስድ ጉዳዩን ቢሰውረው ወይም ቢዘጋው እና/ወይም Montgomery County State's Attorney's Office/የስቴት አቃቤ ፅ/ቤት የወንጀል ክስ መመስረት ፈቃደኛ ባይሆንም፣ የነዚህ አይነት ጉዳዮች የቦርድ መመርያዎች፣ የMCPS ደንቦች፣ ውሎች፣ እና/ወይም ሌላ መመርያ መጣስን የሚያካትቱ ስለሆነ፣ OHRD የውስጥ ምርመራ ያካሂዳል። የCPS፣ MCPD ወይም ሌላ የውጭ ወኪል ድርጅት የሚያካሂደው ማንኛውም ምርመራ በእንጥልጥል ላይ እያለ፣ MCPS ምስክሮችን፣ ተጠቂ የሚባሉትን፣ ወይም የተጠረጠሩ አጥቂዎችን ያለ መርማሪ ወኪል ድርጅቶች ፈቃድ ወይም እነሱ ካስቀመጡት ገደብ ውጭ ምርመራ ማካሄድ አይችልም። በተጨማሪ፣ MCPS የውስጥ ምርመራዎችን ማካሄድ ያለበት ምርመራ በማካሄድ ላይ ከሚገኙት የውጭ ወኪል ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በመተባበር መንፈስ እና የውጩ ምርመራ ላይ ጣልቃ የማይገባ ወይም አደጋ ላይ የማይጥል መሆን አለበት።

በMCPS ንብረት ውስጥ የሚከናወኑ፣ እንደ የእጽ ስርጭት ወይም በጦር መሳርያ የመጠቀም የመሳሰሉ ተጠርጣሪ የወንጀል እንቅስቃሴ የሚያካትቱ ሌሎች ወሳኝ ድርጊቶች፣ በቦርድ መመርያና በMCPS፣ MCPD፣ እና School Resource Officer Program/የት/ቤት መገልገያዎች መኮንን ፕሮግራም እና Other Law Enforcement Responses to School-Based Incidents/ሌሎች የህግ ማስከበርያ መገልገያዎች ለት/ቤት የተመሰረቱ ድርጊቶች የሚያካትቱ የካውንቲ ወኪል ድርጅቶች መካከል

በተገባው Memorandum of Understanding ስምምነት መሰረት ለMCPD እንዲመለከቱ ያስፈልጋል።[36] በተጠረጠሩ የወንጀል እንቅስቃሴዎች፣ ምርመራ ከሚያካሂዱ የውጭ ወኪል ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በመተባበር እና የውጭ ምርመራውን በማያሰናክል ዘዴ OHRD የውስጥ ምርመራ ማካሄድ ይችላል።

4. ሌላ የተጠጠረ ጥፋትን የሚያካትቱ ጉዳዮች ሂደት። በሌሎች ጉዳዮች፣ የሚመልከተውን ህግና የMCPSን ደንቦች በመከተል፣ አተዳዳሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ለOHRD ሲያስታውቁ በሞያዊ ዳኝነት መጠቀም አለባቸው። የሰራተኛ እንቅስቃሴዎች ከቀጥታ ተቆጣጣሪ በላይ የዲስትሪክት ባለስልጣን ወቀሳ፣ እገዳ ያለ ክፍያ፣ ወይም ከስራ ስንብት ያስፈልገው ይሆናል ብለው የሚሰማቸው አተዳዳሪዎችና ተቆጣጣሪዎች ጉዳዩን በራሳቸው ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ ሰራተኛ በለሙያ ሰራተኛ ከሆነ፣ ወይም ለሰራተኛው አስተዳዳሪ ወይም የበላይ ሀላፊ (በአብዛኛው የመምርያ ዲሬክተር) ሰራተኛው የድጋፍ ሰጪ አገግሎቶች ሰራተኛ ከሆነ ለOHRD ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ ማስተላለፍ አለበት። OHRD ተቀብሎ መረጃውን ዳግመ እይታ ያደርግበታል፣ ምርመራ ያካሂደል ወይም እንዲደረግ ያዛል፣ እናም በተገኘው መረጃ መሰረት ተፈላጊውን የሆነ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንዲወሰድ ያደርጋል። አስተዳዳሪው ወይም አለቃው የሰራተኛው ስነምግባር በሙያዊ እድገት ስርአት ወይም በሰራተኛ ዲሲፕሊን ቅደም ተከተል መሰረት መያዝ እንዳለበት ጥያቄ ካለው/ካላት፣ አስተዳዳሪው ወይም አለቃው የOHRDን Performance Evaluation and Compliance Unit/የአፈፃፀም ግምገማና እሽታ ክፍል (PECU) መገናኘት አለበት። በቂ ክሂሎት ወይም እውቀት ባለመኖሩ፣ በአንድ ሰራተኛ የስራ ድርሻዎች አፈፃፀም የማያስደስቱ ሆኔታዎች ሲያጋጥሙ፣ በዘልምድ በሞያዊ እድገት ስርአት በኩል መፈታት አለባቸው፣ እናም ሰራተኛው አጥጋቢ የአፈፃፀም ደረጃ ለማግኘትና ለመንከባከብ ስኬታማ ካልሆነ ውጤቱ ከስራ መሰናበት ሊሆን ይችላል። ጉዳዮች በሙያዊ እድገት ስርአት ወይም በዲሲፕሊን ሂደት ሊታዩ በሚቻልበት ሁኔታ፣ MCPS አንዱን ሂደት ከአንዱ አማርጦ የሚጠቀምበት ግዴታ የለም። ከሰራተኛ የህብረት ተደራዳሪ ከፍሎች አንዱ አባላት የሆኑ ሰራተኞች በምርመራው ወቅት፣ በያንዳንዳቸው የጋራ ድርድር ስምምነት መሰረት፣ በሰራተኛ ማህበራቸው አማካይነት የመወከል መብት አላቸው። አስተዳዳሪዎች ወይም ተቆጣጣሪዎች ስለ የውክልና መብት ጥያቄዎች ካላቸው፣ PECUን ወይም Department of Association Relations/የምህበር ግንኙነቶች መምርያን ማግኘት አለባቸው።

5. የአስተዳደር ፈቃድ ተገቢ ያልሆነ ስነምግባር ጥርጣሬ በአንድ ሰራተኛ፣ ጥርጣሬው እስከሚጣራ ድረስ እሱን ወይም እሷን በአስተዳደራዊ ፈቃድ ለማስቀመጥ በቂ ምክንያት ነው። ጉዳዮች በግለሰብ ደረጃ ይገመገማሉ፣ እናም

ምርመራ፣ ወይም ለተጠረጠረው ሀላፊነት የጎደለው ስነምግባር መደጋገም (ለምሳሌ፣ ጥርጠራው የፋይናንስ በልሽውና ከሆነና ግለሰቡ የMCPS ግንዘቦች የሚያንቀሳቅስ ከሆነ)፣ ቁልፍ ታሳቢ የሰራተኛው በስራው ቀጣይ መኖር ለተማሪዎች ወይም ለሰራተኞች እምቅ አስጊነት ነው። በMCPS ደንብ JHC-RA መሰረት፣ የልጅ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ጥርጣሬ ርእስ የሆነ የMCPS ሰራተኛ፣ ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ አስፈላጊ የሚያደርገው ትርጉም ያለው መረጃ ከሌለ፣ የአስተዳደር ፈቃድ ላይ እንዲቆይ ይደረጋል። ሰራተኞች የአስተዳደር ፈቃድ ላይ እንዲቆዩ ሲደረግ፣ ወደ MCPS ኢሜይል ወይም ሌላ የመገናኛ ቴክኖሎጂ መዳረሻቸውን ለመወሰን እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው።

## የተከለከለ የወንጀል ስነምግባር

ከMCPS የዲሲፕሊን ስርአት በተጨማሪ፣ ለተወሰነ መጥፎ ድርጊት ሰራተኛው/ዋ የወንጀል ክስ ሊያጋጥመው/ማት ይችላል። እነዚህ የወንጀል ስነስርአቶች በሰራተኛው/ዋ የMCPS ቀጣይ ሰራተኛነት ተፅእኖዎች ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ በAnnotated Code of Maryland የትምህርት አንቀፅ ክፍል 6-113 መሰረት፣ MCPS ሳያውቅ አንድ *ፆታዊ* ጥቃቶች፣ የልጅ *ፆታዊ* ማጎሳቆል፣ እና የሁከት ወንጀሎች የሚያካትት በወንጀል የተፈረደበት ወይም ተከሶ በጥፋቱ ያመነ ሰራተኛ ሳይታወቅ ሊቀጥር ይችላል።[37] በተጨማሪ፣ የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ በተወሰኑ የወንጀልና ሌላ መጥፎ ድርጊት በሚያካትቱ ሁኔታዎች በስቴት የተሰጠ የአስተማሪነት ወይም ሌላ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ሊያነሳው ይገደዳል።[38]

MCPS ሁሉም የሰራተኛ አባሎች ከታሰሩ ወይም በMCPS ደንብ GCC-RA፣ *Staff Self-Reporting of Arrests, Criminal Charges, and Convictions/የመታሰ*፣ የወንጀል ክሶች፣ እና የፍርዶች ሰራተኛ በራስ *ዘገባ ማቅረብ* በተዘረዘሩት በወንጀል ከተከሰሱ፣ እንዲሁም በማንኛውም ተከታይ የወንገል ሂደት ቃል መስጠት ራሳቸው ዘገባ ማቅረብ አለባቸው። በራስ ዘገባ የማቅረብ ግዴታ ለሁሉም ተማሪዎችና ሰራተኞች ሰላማዊና አስተማማኝ አካባቢ ለማቅረብ MCPS ያለውን ግዴታ ያንፀባርቃል፣ እናም ከሜሪላንድ ህግ፣ የሜሪላንድ አኖቴትድ ኮድ የትምህርት አንቀፅ ክፍል 6-113 ጨምሮ፣ ማክበርን ያራምዳል። ይህ ግዴታ ለእስራትና ለወንጀለኛ ክሶች፣ እንዲሁም የማናቸውም የወንጀለኛ ቅደም ተከተል ቃል ምዝገባ ላይ፣ ከኦክቶበር 1፣ 2016 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

# ጥያቄዎችና ተጨማሪ መረጃዎች

የMCPS ሰራተኞች ስለዚህ የስነምግባር ኮድ ትርጉም ወይም አተረጓጎም ጥያቄዎች ካሏቸው ወይም ለተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆን፣ ከርእሰመምህራቸው ወይም ከአማካሪያቸው ጋር መወያየት አለባቸው። አስተዳዳሪዎች ወይም ተቆጣጣሪዎች ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሏቸው፣ PECU/OHRDን፣ በ301-279-3361፣ ወይም Department of Association Relations/የማህበራት ግንኙነት መምርያን በ301-279-3511 መገናኘት አለባቸው።

በተጨማሪ፣ ሰራተኞች የሚመለከታቸውን የሰራተኛ ማህበር አባላትን ለምክርና ለእርዳታ መገናኘት ይችላሉ።

የግርጌ ማስታወሻ

[1] ተጨማሪ መረጃ በMCPS ድርጣብያ፣ በwww.montgomeryschoolsmd.org ይገኛል። የሰራተኛ የስነምግባር ደንብ ከተማሪዎች የMCPS ስነምግባር ደንብ የተለየ ነው።

[2] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ BBB ተመልከቱ፣ ግብረገብ፣ እና የMCPS ደንብ GCA-RA፣ *Employee Conflict of Interest/የሰራተኛ የጥቅም ግጭት ተመልከቱ*።

[3] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ JOA-RA፣ *Student Records/የተማሪ* ዘገባዎች ተመልከቱ።

[4] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ DIE-RA፣ ጉዞ ለMontgomery County Public Schools (MCPS) ጉዳዮችን ተመልከቱ።

[5] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ GCB-RA፣ *Reporting and Handling Fraudulent Actions by MCPS Employees, Agents, or Contractors/ በMCPS ሰራተኛ፣ ወኪሎች፣ ወይም ስራ ተቋራጮች የሚፈፀሙ የሙስና ድርጊቶች ዘገባና አያያዝ* ተመልከቱ። ማጭበረበር፣ መባከን፣ ወይም ማጎሳቆልን ስም ሳያስታውቁ ለማመልከት MCPS የአስቸኳይ ጥሪ የቴሌፎን መስመር ያቀርባል፣ ለሰራተኞች ቅሬታዎች እና ከቂምበቀሎች፣ ወይም በቀና መንፈስ ስላጋለጡ ከጥቃት ለመዳን ማረጋገጫ ማግኛ ጎዳና ይሆናቸው ዘንድ ሰራተኞች ማንነታቸው እንዲሸፈን ካልፈለጉ ቅሬታዎቻቸውን ከተቆጣጣሪዎቻቸው ወይም ከሌሎች መሪዎች ከ ት/ቤታቸው ወይም መመርያቸው ጋር መጋራት አለባቸው። ተጨማሪ መረጃ በ*www.montgomeryschoolsmd.org/departments/fraudhotline/* ይገኛል።

[6] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ IGN፣ በ*Montgomery County Public Schools አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና የሌላ እፅ አጠቃቀምን መከለከልን፣ እና የMCPS ደንብ COF-RA፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች እፆች በMCPS ንብረትን* ተመልከቱ። የአልኮል አጠቃቀም በMCPS ንብረት የተከለከለ ነው ለተወሰኑ ሁኔታዎች በቦርድ ሊፈቀድ ካልተቻለ በስተቀር።

[7] MCPS የሚያጠቃልለው ማንኛውንም ት/ቤት ወይም ሌላ መገልገያ፣ የMCPS ንብረት የሆኑ ወይም በሱ የሚተዳደሩ ቦታዎችን፣ እና አውቶቡሶች እና ሌሎች

የMCPS ተሽከርካሪዎች፣ እና በMCPS ስፖንሰር የሆኑ ተማሪዎችን የሚያካትቱ እንቅስቃሴዎች መገልገያ ወይም ቦታን ያጠቃልላል።

[8] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ IGT-RA፣ *User Responsibilities for Computer Systems, Electronic Information, and Network Security/የተጠቃሚ ሀላፊነት በኮምፒውተር ስርአቶች፣ የኤሌክትሮኒክ መረጃዎች፣ የአውታረ መረብ ደህንነት* ተመልከቱ።

[9] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ ILA-RA፣ *Assessments with Security and Reporting Requirements/ግምገማዎች ከደህንነትና የዘገባ አቀራረብ ግዴታዎች* ተመልከቱ።

[10] MCPS ሁሉም ሰራተኞች ከታሰሩ ወይም በMCPS ደንብ GCC-RA፣ *የእስራቶች፣ የወንጀል ክሶች፣ እና ፍርጃዎች በራስ ስለማስታወቅ* በተዘረዘሩት በወንጀል ከተከሰሱ፣ እንዲሁም የተከታይ ወንጀል ሂደት የማሃላ ቃል ራሳቸው እንዲያመለክቱ ይጠይቃል። ይህ ግዴታ ከኦክቶበር 1፣ 2016 በኋላ ለሚደርሱ እስራቶች፣ የወንጀል ክሶች፣ እንዲሁም ከወንጀል ሂደት ቃለ መሃላዎች ላይ ተግባራዊነት አለው።

[11] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ KEA፣ *Political Campaigns and Political Materials/የፖለቲክ ዘመቻዎችና የፖለቲካ ቁሳቁሶች ን*፣ እና የMCPS ደንብ KEA-RA፣ *Participation in Political Campaigns and Distribution of Campaign Materials/ተስትፎ በፖለቲካ ዘመቻዎችና የፖለቲካ ቁሳቁሶች ስርጭትን* ተመልከቱ።

[12] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ IPD-RA፣ T*ravel-Study Programs, Field Trips and Student Organization Trips/የጉዞ ጥናት ፕሮግራሞች፣ የመስክ ጉዞዎችና የተማሪ ድርጅት ጉዞዎችን* ተመልከቱ።

[13] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCAAP ስምምነት አንቀፅ 22Fን፣ የMCEA ስምምነት አንቀፅ 111Aን፣ እና የSEIU ስምምነት አንቀፅ 35Cን ተመልከቱ።

[14] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ BBB፣ ግብረገብ፣ እና የMCPS ደንብ GCA-RA፣ *Employee Conflict of Interest/የሰራተኛ የጥቅም ግጭትን* ተመልከቱ።

[15] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ BBB፣ ግብረገብ፣ እና የMCPS ደንብ GCA-RA፣ *Employee Conflict of Interest/የሰራተኛ የጥቅም ግጭትን* ተመልከቱ።

[16] ለተጨማሪ መረጃ፣ የBoard *መመርያ* BBB፣ *ግብረገብ*፣ እና የMCPS ደንብ GCA-RA፣ *Employee Conflict of Interest/የተማሪ የጥቅም ግጭት* ተመልከቱ።

[17] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ COE-RA፣ *Weapons/የጦር መሳርያዎች* ተመልከቱ።

[18] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያዎች ACA፣ *Human Relations/ሰብአዊ ግንኑነቶች*፣ ACB፣ *Nondiscrimination/አድልዎ-አለማድረግ*፣ እና JHF፣ *Bullying, Harassment, or Intimidation/ማሸማቀቅ፣ ማዋከብ፣ ወይም ማስፈራራት*፣ እና የMCPS ደንብ ACA-RA፣ *Human Relations/ሰብአዊ ግንኑነቶች*፣ እና ደንብ JHF-RA፣ *Bullying, Harassment, or Intimidation/ማሸማቀቅ፣ ማዋከብ፣ ወይም ማስፈራራትን* ተመልከቱ።

[19] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ JHC፣ Child Abuse and Neglect/የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት፣ እና የMCPS ደንብ *JHC-RA፣ Reporting and Investigating Child Abuse and Neglect/የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ከማክበር ሰላምታም ጋር አቀራረብ* ተመልከቱ።

[20] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያዎች ACA፣ *Human Relations/ሰብአዊ ግንኑነቶች*፣ ACB፣ *Nondiscrimination/አድልዎ-አለማድረግ*፣ እና JHF፣ *Bullying, Harassment, or Intimidation/ማሸማቀቅ፣ ማዋከብ፣ ወይም ማስፈራራት*፣ እና የMCPS ደንብ ACA-RA፣ *Human Relations/ሰብአዊ ግንኑነቶች*፣ እና ደንብ JHF-RA፣ *Bullying, Harassment, or Intimidation/ማሸማቀቅ፣ ማዋከብ፣ ወይም ማስፈራራት*። ተጨማሪ መረጃ፣ ተማሪዎች ከአድልዎ፣ ማሸማቀቅ፣ ወይም ከወከባ ነፃ ሆነው የሃይማኖታቸውን እምነቶች የመግልፅ መብት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በተተለመው፣ በMCPS G*uidelines for Respecting Religious Diversity/ሀይማኖታዊ አይነተ-ብዙህነትን የማክበር መመርያዎች* ህትመት ይገኛል።

[21] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ JHF፣ *Bullying, Harassment, or Intimidation/ማሸማቀቅ፣ ማዋከብ፣ ወይም ማስፈራራት*፣ እና የMCPS ደንብ JHF-RA፣ *ማሸማቀቅ፣ ማዋከብ፣ ወይም ማስፈራራትን ተመልከቱ*።

[22] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ JHC፣ *Child Abuse and Neglect/የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት*፣ እና የMCPS ደንብ JHC-RA፣ *Reporting and Investigating Child Abuse and Neglect/የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኝነት ዘገባ አቀራረብ* ተመልከቱ። እባካችሁ በዚህ የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ የተዘረዘሩ የማይገባ ስነምግባር ምሳሌዎች፣ በተወሰኑ ሁኔታዎች፣ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት ሊይዙ እንደሚችሉ አስተውሉ። በMCPS ደንብ JHC-RA መሰረት፣ ማጎሳቆል እንደሚከተለው ይተረጎማል፡-

- ማንኛውም አካላዊ ቁስል፣ የማይታይም ቢሆን፣ ወይም የልጅ ወይም የደካማ አዋቂ የአእምሮ ጉዳት፣ በልጁ/ጂቱ ወይም በደካማ አዋቂ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ የጥበቃ ወይም የእንክብካቤ ሀላፊነት ባለው ማንኛው(ዋ)ም ግለሰብ የልጁ/ጂቱ ወይም የደካማ አዋቂው ጤና ወይም ደህንነት ተጎድቷል ወይም ለመጎዳት የተጨበጠ አደጋ ላይ ነው በሚያሰኝ ሁኔታ።
- ልጅን ወይም ደካማ/vulnerable አዋቂን የመንከባከብ ዘላቂ ወይም ጊዚያዊ ጠባቂነት ወይም ሀላፊነት ባለው በማንኛውም ግለሰብ ላይ የተፈፀመ ማንኛውም የፆታ ተግባር ወይም ተግባሮች (አካላዊ ጉዳቶች ይድረሱም አይድረሱም)፣ የዘመድ የፆታ ግንኙነት፣ አስገዳጅ የፆታ ግንኙነት፣ ወይም በማንኛውም ደረጃ የፆታ ጥቃት፣ ግብረ ሶዶም ወይም ከተፈጥሮ ውጭ የፆታ ልምዶችን የሚጨምር ነገር ግን በነዚህ ያልተወሰነ። ፆታዊ አመፅ ወይም መጠቃት የሚያካትተው፣ ነገር ግን በዚህ ሳይወሰን፣ አላግባብ መጋለጥ፣ የፆታ ብልት/ተግባር የማየት ጉጉት፣ መሳም፣ በእጅ መዳሰስ፣ ፆታዊ መቀራረቦች፣ በማንኛውም ደረጃ የሚፈፀም የፆታ ወንጀል፣ አስገድዶ መድፈር፣ ግብረ ሶዶም፣ ሴተኛ አዳሪነት፣ በሰው መነገድ፣ ወይም የግብረስጋ ግንኙነት ትርእይት፣ ፎቶግራፍ፣ ፊልም ማንሳት መፍቀድ፣ ማበረታታት፣ ወይም መሳተፍ፣ ወይም ልጅን ወይም ደካማ አዋቂን ከህግ ውጭ አድርጎ ማሳየት፣ ወይም አንድን ልጅ ወይም አንድን ደካማ አዋቂ ከለየለት/የተመዘገበ ፆታዊ አጥቂ አብሮ እንዲኖር ወይም በደምበኛነት አካባቢው እንዲገኝ መፍቀድ።

በMCPS ደንብ JHC-RA መሰረት፣ ቸልተኝነት የሚተረጎመው አንድን ልጅ ወይም ደካማ አዋቂ ያለተመልካች ጥሎ መሄድ ወይም ተገቢ እንክብካቤ ወይም ትኩረ ያለማድረግ ድክመት፣ ወይም በወላጅ፣ አሳዳጊ/ጠባቂ፣ ጉዲፈቻ ወላጅ፣ ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ አባል፣ ጎረቤት፣ የMCPS ሰራተኛ፣ በጎ-ፈቃደኛ ወይም ስራ ተቋራጭ፣ ስልጣን ላይ የሚገኝ/የምትገኝ ግለሰብ፣ ወይም የልጅ ወይም የደካማ አዋቂ ሌላ ዘላቂ ወይ ጊዜያዊ የእንክብካቤ ወይም የጥበቃ ወይም የመቆጣጠር የሚከተሉትን በሚያመልክቱ ሁኔታዎች—

- የልጁ/ጂቱ ወይም የደካማ አዋቂው/ዋ ጤና ወይም ደህንነት ተጎድቷል ወይም በተጨባጭ አደጋ ስጋት ለይ መገኘት፣ ወይም
- ለልጁ/ጂቱ ወይም ለደካማ አዋቂው/ዋ የአእምሮ መጎዳት ወይም የአእምሮ ጉዳት ተጨባጭ አደጋ።

[23] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያዎች JGA፣ S*tudent Discipline/የተማሪ ዲሲፕሊን*፣ እና JFA፣ *Student Rights and Responsibilities/የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች*፣ እና የMCPS ደንቦች JGA-RA፣ *Classroom Management and Student Behavior Interventions/የመማርያ ክፍለስተዳደር እና የተማሪ ስነምግባር ጣልቃገብነቶች*፣ JGA-RB፣ *Suspension and Expulsion/ስንብት እና መወገድ* JGA-RC፣ *Suspension and Expulsion of Students with Disabilities/ስንክልና ያላቸው ተማሪዎች እገዳና መወገድ*፣ JFA-RA፣ *Student Rights and Responsibilities/የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች*፣ አና MCPS Student Code of Conduct/የተማሪ ስነምግባር ኮድን ተመልከቱ።

[24] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንብ JGA-RA፣ *Classroom Management and Student Behavior Interventions/የመመርያ ክፍል አስተዳደር እና የተማሪ ስነምግባር ጣልቃገብነቶች* ተመልከቱ።

[25] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያ ABC፣ P*arent and Family Involvement/የወላጅና የቤተሰብ ተሳትፎ*፣ የMCPS ደንብ ABC-RA፣ *Parent and Family Involvement/የወላጅና የቤተሰብ ተሳትፎ* ተመልከቱ።

[26] ለተጨማሪ መረጃ፣ የMCPS ደንቦች ABA-RB፣ *School Visitors/የት/ቤት ጎብኝዎች*፣ እና IRB-RA፣ *Volunteers in Schools/በጎ-ፈቃደኞች በት/ቤት ውስጥ* ተመልከቱ።

[27] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያዎች ACA፣ *Human Relations/የህዝብ ግንኙነቶች*፣ እና ACB *Nondiscrimination/ጸረ አድልዎ ተመልከቱ*።

[28] ለተጨማሪ መረጃ፣ የቦርድ መመርያዎች ACF፣ Sexual Harassment/*ፆታዊ* ወከባ፣ እና ACH *Workplace Bullying/የስራ ቦታ ወከባ*፣ እና የMCPS ደንቦች ACF-RA፣ *Sexual Harassment/ፆታዊ ወከባ*፣ እና ACH-RA፣ *Workplace Bullying/የስራ ቦታ ወከባን* ተመልከቱ።

[29] Annotated Code of Maryland የትምህርት አንቀፅ ክፍል 6-202 መሰረት፣ የምስክር ወረቀት ያላቸው ሰራተኞች ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አምስት የተለያዩ ምክንያቶች በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ሊታገዱ ወይም ሊሰናበቱ ይችላሉ። ብልግና፣ በፅ/ቤት ውስጥ መጥፎ ተግባር፣ Family Law Article/የቤተሰብ ህግ አንቀፅ ክፍል 5-704ን በመጣስ የተጠረጠረን የልጅ ማጎሳቆል አለማስታወቅን ጨምሮ፤ አለመታዘዝ፤ የችሎታ ማነስ፤ እና ሆን ብሎ ስራን ችላ ማለት። እነዚህ የምስክር ወረቀት ያላቸው ሰራተኞች የመታገድ ወይም የመሰናበት አምስት መሰረታዊ

ምክንያቶች በተፈጥሮ ስፋት አላቸው እናም (የእውነታዎችና የሁኔታዎች ክብደት ታሳቢነት የተጠበቀ ሆኖ)፣ ከአያሌ ሌሎች ነገሮች መካከል፣ በቅጥር ወይም ከቅጥር ውጭ እንቅስቃሴዎች በመነሳት በጥፋት ድርጊት መወንጀል ለአሉታዊ የቅጥር እርምጃዎች መሰረት ሊሆኑ ይችላሉ።

30 ለተጨማሪ መረጃ፣ COMAR 13A.06.07.07 (የት/ቤት ተሽከርካሪ አንቀሳቃሾች) እና COMAR 13A.06.07.08 (የት/ቤት ተሽከርካሪ ረዳቶች) ተመልከቱ።

31 የሰራተኛ ስነምግባር ደንብ የሰራተኛ የግልግል የጋራ ህግን እንዲተካ አልታሰበም ወይም በዲስትሪክቱ የህብረት ስምምነት ስር ለተቋቋመ በአግባቡ የተሰየመ የግልግል ዳኛን ማገድ አይችልም።

32 አንድነቱ/The Compact www.montgomeryschoolsmd.org/staff/respect/ ውስጥ ይገኛል።

33 ለተጨማሪ መረጃ፣ www.montgomeryschoolsmd.org/departments/professionalgrowthን ተመልከቱ።

34 የተሟላ የቦርድ መመርያዎች እና የMCPS ደንቦች ጥራዝ በwww.montgomeryschoolsmd.org/departments/policy/ ይገኛል።

35 የትራንስፖርት መመርያ መፅሀፍ በwww.montgomeryschoolsmd.org/departments/transportation/about/jcsbabo.pdf ይገኛል፣ እና በቦርድ እና በSEIU መካከል የህብረት ስምምነት ድርድር በተያያዘ ሁኔታ አገልግሎት ላይ ይውላል።

36 ይህ Memorandum of Understanding/የመግባባት ማስታወሻ በww.montgomeryschoolsmd.org/uploadedFiles/departments/security/SRO-Memorandum-2015.pdf ይገኛል።

37 የAnnotated Code of Maryland የትምህርት አንቀፅ ክፍል 6-113 በሚከተሉት ክስ ቀርቦበት የተፈረደበት ወይም አምኖ መከራከርያ አላቀርብም/nolo contendere (no contest) ያለን ሰራተኛ MCPS እንዳይቀጥር ይከለክለዋል፡-

a. ፆታዊ አመፅ በMaryland Code §3–307 ወይም §3–308 የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሶስተኛ ወይም አራተኛ እርከን/degree ወይም በሌላ ስቴት ህጎች መሰረት በሜሪላንድ ቢፈፀም ኖሮ በወንጀለኛ ህግ የአንቀፅ §3–307 ወይም §3–308 የሚያስጠይቅ ወንጀል፤

b. የልጅ ፆታዊ ማጎሳቆል በወንጀለኛ ህግ አንቀፅ §3-602፣ ወይም በሌላ ስቴት ህጎች መሰረት በሜሪላንድ ቢፈፀም ኖሮ በወንጀለኛ ህግ የአንቀፅ §3–602 የሚያስጠይቅ ወንጀል፤ ወይም

c. አንድ የሁከት ወንጀል በወንጀለኛ ህግ አንቀፅ §14-101 እንደተገለጸ፣ ወይም በሌላ ስቴት ህጎች መሰረት በሜሪላንድ ቢፈፀም ኖሮ በወንጀለኛ ህግ የአንቀፅ §14–101 የሚያስጠይቅ ወንጀል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡- (1) ጠለፋ፣፤ (2) ቤት ማቃጠል አንደኛ ደረጃ፤ (3) አፍኖ መውሰድ፤ (4) ነፍስ መግደል፣ ሆን ተብሎ የተደረገ ሳይሆን፤ (5) ረብሻ መፍጠር፤ (6) አካለ ስንኩል ማድረግ፤ (7) ግድያ፤ (8) አስገድዶ መድፈር (9)ስርቆት/ቅሚያ፤ (10) አስገድዶ መኪና መዝረፍ፤ (11) በመሳርያ አስፈራርቶ መኪና መዝረፍ፤ (12) ፆታዊ ጥቃት በአንደኛ ደረጃ፣ (13) ፆታዊ ጥቃት በሁለተኛ ደረጃ፣ (14) ከባድ ወንጀል ወይም የሁከት ወንጀል ሲፈፀም በእጅ የጦር መሳርያ መጠቀም፤ (15) የልጅ ማጎሳቆል በአንደኛ ደረጃ፣

(16) ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች የፆታ ማጎሳቆል፣ (17) የዚህ ዝርዝር (1) እስከ ቁጥር (16) የተዘረዘሩትን ወንጀሎች መካከል የሆነውን ለመፈፀም መሞከር፤ (18) በወንጀለኛ ህግ አንቀፅ §3-315 ከልጅ ጋር የነበረ ስነምግባር ቀጣይነት፤ (19)ድብደባ በአንደኛ ደረጃ፤ (20) ለመግደል አስቦ መደብደብ፤ (21) ለመድፈር መደብደብ፤ (22) ለቅሚያ መደብደብ፤ (23) በአንደኛ ደረጃ የፆታ ጥቃት ለመፈፀም መደብደብ፤ እና (24) በሁለተኛ ደረጃ የፆታ ጥቃት ለመፈፀም መደብደብ።

[38] በCode of Maryland Regulations/ሜሪላንድ ደንቦች ህግ (COMAR) 13A.12.05.02፣ የሜሪላንድ ስቴት የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ አንድ ግለሰብ ከሚከተሉት አንዱን ከፈፀመ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ለአስተማሪው ወይም ለሌላ ባለሙያ የተሰጠውን የምስክር ወረቀት እንዲያነሳው/እንዲሰርዘው ይገደዳል—

1. የሚከተሉትን በሚያካትት ወንጀል ተከስሶ ጥፋቱን በማመን አልከራከርም/nolo contendere (no contest) ካለ፣ ከፍርድ በፊት በአሞክሮ ከቆየ፣ ወይም ከተፈረደበት—
    a. የልጅ ማጎሳቆል ወይም ቸልተኝነት በሜሪላንድ ስቴት ህግ፣ የወንጀል ህግ በአሞክሮ §§3-601–3-603፣ ወይም በተመጣጣኝ ወንጀል በሌላ ስቴት፣ ወይም
    b. በሜሪላንድ ስቴት ህግ፣ የወንጀል ህግ አንቀፅ፣ §14-101 የሁከት ወንጀል፣ ወይም በተመጣጣኝ ወንጀል በሌላ ስቴት፤ ወይም
2. የልጅ ፆታዊ ማጎሳቆል ከተጋለጠ በኋላ ከተባረረ ወይም በፈቃዱ ከተሰናበተ።

በተጨማሪ፣ COMAR 13A.12.05.02 የሜሪላንድ ስቴት የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ፣ በሚቀጥሉት ሁኔታዎች  ያንድን ባለሙያ የምስክር ወረቀት እንደሁኔታው ማገድ ወይም ማንሳት እንዳለበት አስቀምጦታል—

1. የሚከተሉትን በሚያካትት ወንጀል ተከስሶ ጥፋቱን በማመን አልከራከርም/nolo contendere (no contest) ካለ፣ ከፍርድ በፊት በአምክሮ ከቆየ፣ ወይም ከተፈረደበት—
    a. ለአንድ/ዷት ትህተ እድሜ መበላሸት አስተማፅኦ በማድረግ፤
    b. የሞራል ጭካኔ/እርጉምነት፣ ጥሰቱ የግለሰቡን የማስተማር ብቃትን በቀጥታ የሚያመለክት ከሆነ፤ ወይም
    c. የተከለከለ/የተገታ ነገር ጥሰት በፌደራል ወይም በስቴት ህግ የተገለፀ፣ በሜሪላንድ ለተፈፀመው ለዚህ ጥሰት የተሰጠው ፍርድ በአንቀፅ 41፣ §§1-501–1-507፣ እና በሜሪላንድ ህግ የወንጀለኛ አዋጅ አንቀጽ §5-810 ተግባራዊ ይሆናል፤
2. በፈቃደኝነት ሆን ተብሎ—
    a. ለምስክር ወርቀት ማመልከቻ ላይ የተጨበጠ ማጭበርበር ወይም የመሸሸግ ተግባር መፈፀም፣
    b. የምስክር ወርቀት ማመልከቻ ሲደረግ ስለ ተጨባጭ ነገር ሀሰተኛ መግለጫ /ራፖር ወይም ዘገባ ማህደር ውስጥ ማስገባት፣ ወይም

c. በCOMAR 13A.03.04 የተቀመጡትን የፈተና ሚስጢራዊነት እና የመረጃ ዘገባ መመርያ እና ስርአት መጣስ፤

3. አጭበርብሮ ወይም አታልሎ የምስክር ወረቀት ማግኘት

4. በሜሪላንድ ህግ የቤተሰብ አዋጅ አንቀፅ §5-701 በመጣስ የተጠረጠረ የልጅ ማጎስቆልን ዘገባ አለማድረግ፤

5. አንድን ተማሪ በማንኛውም የት/ቤት ስርአት ውስጥ ወይም ማንኛውንም ከአቅመ አዳም/ሄዋን በታች የሆነን በሚያካትት ጥፋት ጥርጣሬ፣ ወይም በዚህ ደንብ መሰረት የምስክር ወረቀት መታገድ ወይም መነሳት የሚያካትት ጥፋት ጥርጣሬ ማስታወቂያ በኋላ የተባረረ ወይም በፈቃዱ የተሰናበተ፤

6. በዚህ ደንብ መሰረት ለእገዳ ወይም ለመነሳት በቂ በሚሆን ምክንያት በሌላ ስቴት የምስክር ወረቀቱ የታገደ፣ የተነሳ ወይም በፈቃዱ ያስረከበ።

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ROCKVILLE, MARYLAND

በDepartment of Materials Management for the Office of Communications የታተመ
ትርጉም በLanguage Assistance Services Unit • Office of Communications
Copyright © 2016 Montgomery County Public Schools, Rockville, Maryland
0047.17 • Editorial, Graphics & Publishing Services • 9/16 • Amharic • NP